እግዚአብሄርን አስብኩት ደስም አለኝ
ፍቅሩንም አሰብኩት ደስም አለኝ
ምህረቱን አሰብኩት ደስም አለኝ
ቸርነቱን አስብኩት ደስም አለኝ

ሃሌሉያ ታላቅ ነህ ሃሌሉያ (4)
እያሉ ቅዱሳን ሲያደንቁህ ሰምቼ
አብሬአቸው ዘመርኩ በገናን ቃኝቼ
አዎ ከሁሉ በላይ ነህ ከማንም በላይ ነህ
ኢየሱስ የለም የሚመስልህ

ባለጠጋ በገንዘቡ ይመካል
ሰዎችንም በዚሁ ይለካል
በጎተራ ያለው ምርቱ ሳይበላ
በሞት ይጠራል ትቶለት ለሌላ
አንተ ግን ጌታዬ የዘላለም ነህ
ብናመልክህ ታዋጣናለህ (2)

ሃሌሉያ ታላቅ ነህ ሃሌሉያ (4)

ሥልጣን እውቀት አንድ ቀን ይሻራል
የኔ ጌታ ግን እንደገዛ ይኖራል
የዚህ ዓለም ክብር እኔን አያጓጓኝ
ዘላለማዊው ቆይቷል ከገባኝ
ጠቢባን (ኃያላን) ነን ያሉ እንደምን ተሞኙ
የሕይወትን ጌታ ሳያገኙ (2)

ሃሌሉያ ታላቅ ነህ ሃሌሉያ (4)
እያሉ ቅዱሳን ሲያደነቁህ ሰምቼ
አብሬአቸው ዘመርኩ በገናን ቃኝቼ
አዎ ከሁሉ በላይ ነህ ከማንም በላይ ነህ
ኢየሱስ የለም የሚመስልህ

የትም አልሄድ እርዳታን ፍለጋ
አምላክ አለኝ ሁሌ ባለጠጋ
ደስ እያለኝ በቤቱ ኖራለሁ
ምን ጎድሎብኝ ጌታን አግኝቻለሁ
እንዳንተ የሚሆን ስላላገኘን
ቀንም ሌትም እናከብርሃለን
እንዳንተ የሚሆን ስላላገኘን
ዛሬም ነገም እናመለክሃለን
ለዘላለም እናመልክሃለን

ባለኝ አቅም ልዘምር ልበልህ የበላይ
ቃሎቼ ባይመጥኑም ዝም ብዬ ከማይ
ልበልህ የበላይ (2)
የበላይ ነህ የበላይ የበላይ
ሁሉን የረታህ ኤልሻዳይ ኤልሻዳይ ጌታ ኤልሻዳይ

ወደ ሰማይ ወጡ ቢወጡ እንዳንተ እንዳንተ የለም
ምድርንም ዞሩ ቢዞሩ እንዳንተ እንዳንተ የለም
እንዳንተ እንደሌለ አውቀዋል ምሁር ሊቃውንቱ
እጃቸውን ሰጡ ለክብርህ ሊገዙ
የበላይ ነህ የበላይ የበላይ ...